## <u>የእጅግ ከፍተኛ ስራና አገልግሎት ሽልማት አሰጣጥ</u>

# <u>ደንብና ሥርዓት</u>

ሰኔ 24 ቀን 2000 ዓ/ም

## 1. ራእይ፤

በግለሰብም ሆነ በብዙሐን አማካኝነት፤ እርስ በርስ በመረዳዳት፤ እንዲሁም ለአሜሪካና ለውድ ሐገራችን ለኢትዮጵያ የሚጠቅሙ፤ እጅግ አስደናቂ ውጤቶች በዘላቂነትና በአስተማማኝነት የሚያስገኝ በዳላስ ፎርት ወርዝ የሚገኝ የኢትዮጵያውያን ማሕበረሰብ፤

## 2. ዓላማ፤

ዓላማው፤ በዚህ ደንብና ሥርዓት መሠረት፤ ዳላስ ፎርት ወርዝ በሚገኘው ሕበረተሰብ፤ አስደናቂ ውጤቶችን ለማስገኘት፤ ለማበረታታት፤ ለመቀስቀስና ለመሸለም ነው።

## 3. መሠረታዊ መስፈርቶች፤

3.1 ውጤቱ፤ ተቀባይነት በሚኖራቸው ደረጃዎች መሠረት፤እጅግ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው መሆኑ፤

3.2 ለግለሰብ፤ ለማሕበረሰቡ፤ እና/ወይም ለአሜሪካ/ለኢትዮጵያ እንዲሁም በአጠቃላይ ለሰው ልጅ ከፍ ያለ ጥቅም የሚያሰገኝ፤ ምሳሌነት ያለው መሆኑ።

## 4. የውጤቶቹ ዓይነቶች፤

4.1 በዳላስ ፎርት ወርዝ ለሚገኘው የኢትዮጵያ ማሕበረሰብ ጥቅም የሚያሰገኝ እጅግ ከፍተኛ ውጤት፤

4.2 ለአሜሪካ እና/ወይም ለኢትዮጵያ እንደ በጎ አድራጎትና ሌሎች አገልግሎቶችን የመሰለ ዋጋ ያለው እጅግ ከፍተኛ ውጤት፤

4.3 በትምሕርት፤ በምርመራ፤ በሌሎች የኢኮኖሚ፤ የማሕበራዊና የባሕላዊ ጥረቶች እጅግ ከፍተኛ ውጤት፤

4.4 በማሕበራዊ ሥራዎች እጅግ ከፍተኛ የሆነ ረጅም አገልግሎትና ተሳትፎ፤ በተጨማሪ፤ ሌላም በማሕበሩ ቦርድ ውሳኔ የሚያሸልም ውጤት።

## 5. ሽልማቱን ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ፤

5.1 ሽልማቱን ለማግኘት፤ በግለሰብም ሆነ በብዙሐን ተገቢውን ቅጽ በመሙላት፤ ለመረዳጃ ማሕበሩ ማቅረብ ያስፈልጋል።

5.2 ለሽልማቱ ተቀባይ ሆኖ ለመወዳደር፤ በዚህ ደንብና ሥርዓት በተደነገገው መሠረት፤ የማመልከቻ ቅጹን በትክክል መሙላትና የሚያስፈልገውን የማረጋገጫ ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ ያስፈልጋል።

## 6. ማመልከቻዎችን የማጥናት ሥርዓት፤

### 6.1 የጥናትና የመምረጥ ቡድን፤

6.1.1 የመረዳጃ ማሕበሩ ቦርድ፤ መስፈርቶችን በሚገባ አሟልተው፤ ለሽልማቱ የቀረቡትን ማመልከቻዎች የሚያጠናና የሚመርጥ አንድ ቡድን ያቋቁማል።

6.1.2 ቡድኑ አስፈላጊ ከመሰለው፤ አመልካቹን ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል።

6.1.3 ቡድኑ አስፈላጊውን ግምገማ ካደረገ በኋላ የተወዳዳሪዎቹን ውጤት በደረጃ በማስቀመጥ ግኝቱንና የሚያቀርበውን ሃሳብ ያካተተ ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል።

### 6.2 የቦርዱ ውሳኔ፤

6.2.1 ቦርዱ፤ የጥናትና የመምረጥ ቡድኑ ያቀረበለትን ውሳኔ መርምሮ ከሁሉም የተሻሉትን ለሽልማቱ ብቁ የሆኑትን ይመርጣል።

6.2.2 የቦርዱ ውሳኔ ጽኑና የመጨረሻ ይሆናል።

6.2.3 የቦርዱ ውሳኔ፤ ተገቢ በሆኑ የመገናኛ ብዙሐን ይገለጻል።

7. ሽልማቱ፤

7.1 የሽልማቱ ዓይነት፤ ለአሸናፊው የሚበረከቱ፤ የምስክር ወረቀት፤ ሌሎች ጥቅማ-ጥቅሞች እንዲሁም ልዩ ሰሌዳ ይሆናል።

7.2 የሽልማቱ ስነ-ሥርዓት የሚከናወነው "በኢትዮጵያ ቀን በዓል"ጊዜ ይሆናል። ሆኖም የተለየ አስፈላጊ ሁኔታ ከተፈጠረ ቦርዱ ተገቢ በሆነ በሌላ ክብረ በዓል ሊያደርገ ይችላል።

7.3 ማሕበሩ ስለ ተሸላሚዎቹ ልዩ መግለጫ አዘጋጅቶ ተገቢ በሆኑ የመገናኛ ብዙሐን ያሰራጫል።

8. የጊዜ ገደብ፤

8.1 ማሕበሩ፤ ለሽልማቱ አመልካቾችን የሚጋብዝ መግለጫ እ.ኤ.አ በጁን 30 ወይም ከዚይ ቀን በፊት ያወጣል።

8.2 ማመልከቻዎች እ.ኤ.አ እስከ ጁላይ 15 መቅረብ አለባቸው።

8.3 የጥናትና የመምረጥ ቡድኑ ተግባሩን እ.ኤ.አ እስከ ኦገስት 15 መፈጸም አለበት።

8.4 ቦርዱ የሽልማት አሸናፊዎቹን እ.ኤ.አ እስከ ኦገስት 22 ይመርጣል።

8.5 ማሕበሩ አሸናፊዎቹን እ.ኤ.አ እስከ ኦገስት መጨረሻ በይፋ ያስታውቃል።

9. ደንቡ ሥራ ላይ የሚውልበት፤

ይህ ደንብና ሥርዓት እ.ኤ.አ ከጁላይ 1፤ 2008 ዓ/ም ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል።

10. ማሻሻያዎች፤

የማሕበሩ ቦርድ ተገቢ ሆኖ በሚያገኘው መሠረት፤ ይህ ደንብና ሥርዓት ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊሻሻል ይችላል።